በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን።

ይህ ጽሁፍ በዕቅበተ እምነት ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ የፌስቡክ እና የቴሌ ግራም ግሩፓችን ላይ "በእንተ ሰማንያ አሃዱ" በሚል ርእስ በአምስት ክፍል የቀረበው ጽሁፍ አንድ ላይ ተሰብስቦ በ PDF የቀረበበት ነው።

የ facebook እና የ telegram ገፃችን

በ facebook: ዕቅበተ እምነት ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

በ telegram: https://t.me/ekbetemnet

በእንተ ሰማንያ አሃዱ (ክፍል-1)

የሰማንያ አሃዱ መጻሕፍት ምንጮች እና ቀኖናት

በውስጥ ገጾች፡-

- ✓ ጥያቄያዊ መልእክቶች ለፕሮቴስታንታውያን
- ✓ መጽሐፍ ቅዱስ ለመጻሕፍቱ እንደ ምንጭነት ይጠቀሳል።
- ✓ የሰባ ሊቃናት(Septuagint) ትርጉም እና ስብስብ፤ ማሶሬቲክ ቴክስት(Masortic Text)
- ✓ የሐዋርያውያት ቀኖና (Apostolic Canons) እንደ ምንጭነት ይጠቀሳል።
- ✓ ሲኖዶሳውያት ጉባኤዎች እና የቤተክርስቲያን አባቶች(Church Fathers) እንደ ምንጭነት ይጠቀሳሉ።
- ✓ የሐዲስ ኪዳን የሥርዐት መጻሕፍት ምንጮች

ዕቅበተ እምነት ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

መግቢያ

- ✓ የቤተክርስቲያን አስተምህሮ መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ምንም እንኳን ኦርቶዶክሳዊው እስቤ መጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛው የክርስትና አስተምህሮ መመሪያና ምንጭ ነው ባይልም መጽሐፍ ቅዱስ ለቤተክርስቲያን መተኪያ የሌለው የጽሁፍ ሀብቷ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛው የክርስትና አስተምህሮ መመሪያና ምንጭ አይደለም ያልነው በሥርአተ አምልኮና በቃል የተላለፈው ትውፊት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጎን ለጎን አብሮ ስለሚያገለግል ነው። የጽሁፉ ሀሳብ መጽሐፍ ቅዱስን በሚመለከት ስለሆነ የቃል ትውፊትን በሚመለከት እራሱን በቻለ ርእስ እንመጣበታለን። መጽሐፍ ቅዱስ ለክርስትና አስተምህሮ መሠረት ነው የሚለው በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነት ቢኖረውም በውስጡ ስላሉት የመጽሐፍት ብዛት ግን ልዩነት መኖሩ የታወቀ ነው። በተለይም ፕሮቴስታንታውያን ከሉተር የተሃድሶ እንቅስቃሴ በኃላ እንደ አዲስ የተሰራውን 66ት መጽሐፍት ያለውን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሚቀበሉ በኦርቶዶክሳውያን ዘንድ ያሉ (እነርሱ ጋር የሌሉትን) መጽሐፍት ሲተቹ ይታያሉ። ለአብነትም በቴዎድሮስ ደመላሽ "ሰማንያ አሃዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን" የሚለውን መጽሐፍና "ኦርቶዶክስ መልስ ካላት እኛም ጥያቄ አለን" በሚል የተዘጋጀውን ቪሲዲ መጥቀስ ይቻላል። ይህንን መሠረት በማድረግ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ስላለው በተለምዶ ሰማንያ አሃዱ ስለሚባለው መጽሐፍ ቅዱስ ከስር ከመሠረቱ በመመልከት ለጠያቂዎች ምላሽ አዘጋጅተናል።

=>>>እንደ መንደርደሪያ (አጠቃላይ ጥያቄያዊ መልእክቶች ለፕሮቴስታንታውያን)

1. መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ጊዜና ቦታ የተጻፈ መጽሐፍ እንደሆነ ይታወቃል። በተለይም የሀዲስ ኪዳን መጽሐፍት በተጻፉበት ወቅት ሌሎች ሀሰተኞች መጽሐፍት (ψευδεπγραφα/Peudepigraha) ስለነበሩ እውነተኞችን መጽሐፍት ከሀሰተኞች ለመለየት የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና (Biblical Canonization) መንገድ ተጠቅመዋል። በዚህ የቀኖና ሂደት ውስጥ የተሳተፍት የጥንቷ ቤተክርስቲያን አባቶች (Early Church Fathers) ነበሩ። እነዚህ አባቶች በክህነት የሚያምኑና እራሳቸውም እስከ ድጵስና ደረጃ የደረሱ ነበሩ። ይህ ከሆነ ዛሬ ላይ ያሉ በመጽሐፍ ቅዱስ እናምናለን የሚሉ የተለያዩ በክርስትና ስም ያሉ የእምነት ድርጅቶች (ፕሮቴስታንታውያን፣ ጅሆቫ ዊትነስ፣ አንሊ ጂሰሶች) የጥንቷ ቤተክርስቲያን አባቶች ሰፍረው እና ለክተው የሰጧቸውን መጽሐፍት ነው የሚጠቀሙት ማለት ነው። እኛም የቤተክርስቲያን አባቶች በምሥጢራተ ቤተክርስቲያን፣ በነገረ ክርስቶስ፣ በምሥጢረ ሥላሴ፣ በነገረ ማርያም፣ በነገረ ድኅነት፣ በነገረ ቤተክርስቲያን ያስተማሩትን ትምህርቶች ለምን አትቀበሉም? ብለን እንጠይቃለን።

እውነተኞችን መጽሐፍት ከሀሰተኞች ለይተው ቀንነው በአንድ ጥራዝ የሀይማኖት መመሪያ የሆነውን መጽሐፍ ከተቀበላቹ ሙሉ ትምህርታቸውን ለምን አትቀበሉም? ለማለት እንወዳለን።

2. ሉተር ከካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሲወጣ ከጀመራቸው "የብቻ ትምህርቶች" አንዱ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ (Scripture alone) ነው። ይህ አመለካከት ዛሬ ላይ ባሉ የፕሮቴስታንት ዲኖሚኔሽኖችም ዘንድ የሚንጸባረቅ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በውስጡ ምን ያህል መጽሐፍት እንዳሉት አይዘረዝርም። ጸሀፊያቸው ማን መሆኑን እንኳ የማይናገሩት የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት ራሳቸውን በራሳቸው አያረጋግጡም። ለምሣሌ የማቴዎስ ወንጌልን እንውሰድ። የማቴዎስ ወንጌል የተጻፈው ከ 12ቱ ሐዋርያት አንዱ በሆነው በማቴዎስ ስለ መሆኑ አንድም ቦታ ላይ እንኳ አይናገርም። እንዲያውም በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ዘመን በማቴዎስ ስም ይሰራጭ የነበረው መጽሐፍ የማቴዎስ ወንጌል ብቻ አልነበረም። ማቴዎስ ወንጌላዊ ጽፎታል ተብሎ ይሰራጭ የነበረ "የተከራካሪው የቶማስ መጽሐፍ- The book of the contender" የሚባል መጽሐፍም ነበር። የማቴዎስ ወንጌልን ከዚህ አይነቱና ሌሎች መጽሐፍት ቱውፊትን ካልተጠቀሙ እንዴት መለየት ቻሉ?

3. ለመጀመሪያ ጊዜ ዛሬ ላይ ፕሮቴስታንቶች በሚቀበሏቸው መልኩ 66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ የተቀነነው (የተዘጋጀው) ከሉተር በኃላ ነው። ለአብነት ብንመለከት:-

=>>> ሶስቱ ሲኖዶሳውያት ቀኖና ፕሮቴስታንቶች የማይቀበሏቸውኝን መጽሐፍት ይዘዋል።

1. 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት 85ኛ ቀኖና (Canons of the apostles) [1]:- ፕሮቴስታንቶች የማይቀበሏቸውን ከብሉይ ኪዳን መቃብያን መጽሐፍትን፣ ከሀዲስ ኪዳን መልእክታተ ቀለሜንጦስን አካቶ ይዟል። በአንጻሩ ደግሞ የዮሐንስ ራእይን አያካትትም።

2. ቀኖናት ዘሎዶቅያ/Council of Laodicea [2]:- የሎዶቅያ 60ኛ ቀኖና ፕሮቴስታንቶች የማይቀበሏቸውን መጽሐፈ ባሮክ እና ተረፈ ኤርሚያስን ይዟል በአንጻሩ ደግሞ የዮሐንስ ራእይን አያካትትም።

3. ቀኖናት ዘቅርጣግ (Codex Canonum ecclesiae africanae) [3] በመባል ይታወቃል። ይህ ቀኖና ፕሮቴስታንቶች የማይቀበሏቸውን መጽሐፈ ጥበብና የመቃብያን መጽሐፍትን ይዟል።

---

[1]Michael D. Marlowe. "The "Apostolic Canons" (about A.D. 380)" . Bible Research . Archived from the original on 29 August 2010. Retrieved 2 September 2010.

[2] Council of Laodicea at bible-researcher.com . Retrieved 2011-10-05.

[3]http://www.bible-researcher.com/carthage.html

- ✓ በቤተክርስቲያን አባቶች በግል ደረጃ የተቀነኑ ቀኖናዎች ስንመለከትም ዛሬ ላይ ፕሮቴስታንት እጅ ካለው የተለዩ ሆነው እናገኛቸዋለን። ለምሣሌ ቅዱስ አትናቴዎስ በ 367ዓ.ም በላከው የፋሲካ መልእክቱ 39ኛ ላይ የመጽሐፍትን ዝርዝር በቀኖና መልክ አስቀምጧል። [4]ቅዱስ አትናቴዎስ በዘረዘራቸው ውስጥ መጽሐፈ ባሮክና ተረፈ ኤርሚያስ(ፕሮቴስታንቶች የማይቀበሏቸው) ተካተው ሲገኙ መጽሐፈ አስቴር (ፕሮቴስታንቶች የሚቀበሉት) አልተካተተም።

- ✓ እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ ዛሬ 66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው እውነተኛ፣ ሌሎች መጽሐፍት ሀሰተኞች/ተቀባይነት የሌላቸው የሚለው ሀሳብ እንዴት ተቀባይነት ይኖረዋል? ከየትኛው ታሪካዊ የቀኖና ሂደትስ አገኙት?በእርግጥም ከጥንት የቤተክርስቲያን አባቶች ሉተር በልጦባቸው ይህን አድርገዋል።

[የዲዩትሮካኖኒካል/Deuterocanonical መጻሕፍት ምንጮች]

- ✓ በኦርቶዶክስና በካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙ በፕሮቴስታንቶች ዘንድ የማይገኙ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ዲዩትሮካኖን(Deuterocanon) ተብለው ሲጠሩ ሁለተኛ የቀኖና መጻሕፍት ማለት ነው። በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ደግሞ ፕሮቶካኖን(Protocanon) ተብለው ሲጠሩ የመጀመሪያ ቀኖና መጻሕፍት ማለት ነው። ፕሮቶካኖን እና ዲዩትሮካኖን የሚለው ቃል ቅደም ተከተልን (Chronological Order) የሚያሳይ እንጂ በመጻሕፍቱ መካከል ለየቅል የደረጃ ልዩነት እንዳለ (Distinction in Status) የሚገልጽ አይደለም። [5] ይህም ማለት ዲዩትሮካኖኒካል የተባለቡት ዋናው መክንያት በቀኖና የተመዘገቡበትን የታሪክ ምእራፍ ለማመልከት ነው።

- ✓ የመጀመሪያዎቹ የብሉይ ኪዳን ቀኖና መጻሕፍት(Protocanonical Books) በእስራኤል የመመለስ ዘመን ካህኑና ጸሀፊው ዕዝራ በሠራው ቤተ መጻሕፍት ውስጥ አስቀምጧቸዋል። በዚህ ወቅት የተሰበሰቡት መጻሕፍት በአይሁድ እጅ የተገኙት ብቻ ነበሩ። በሳምራውያን እና በኤሴያውያን እጅ የነበሩ መጻሕፍት በወቅቱ አልተሰበሰቡም። [6] በሁለተኛ መቃብያን እንደ ተጻፈው ነህምያ ቤተ መጻሕፍት ባቋቋመ ጊዜ የነገሥታትንና የነብያትን መጻሕፍት የዳዊት መዝሙራትና የነገሥታትን ደብዳቤዎች አሰባስቧል። ዕዝራና ነህምያ በሌሎች የአይሁድ ክፍሎች (ሳምራውያንና ኤሴያውያን) እጅ የነበሩትንና ከእነርሱ በኃላ የተጻፉትን መጽሐፍት አላሰባሰቧቸውም።

---

[4]የሰማንያ አሃዱ መጽሐፍት ምንጮች እና ቀኖናት-ዲበኩሉ ዘውዴ ገጽ 52

[5] Catholic Encyclopedia, Canon of the Old Testament

[6]The Bible through the Ages p-127

- ✓ ሁለተኛዎቹ የብሉይ ኪዳን የቀኖና መጻሕፍት (Deuterocanonical Books) ከእዝራና ከነህምያ በኃላ የተጻፉ ወይም ቀድመው ቢጻፉም በኃላ ተሰባስበው ወደ ቀኖና የገቡ መጻሕፍት ናቸው። እስራኤላውያን በግብጽ በባቢሎንና በፋርስ በተደጋጋሚ በደረሰባቸው ስደት የተነሳ መጽሐፍት ተበታትነው ይገኙ ነበር። በተለይም ከ 2ኛው ክ/ዘመን በኃላ ወደ ቁምራን ዋሻ (ሙት ባሕር አካባቢ) መሰባሰብ የጀመሩት ኤሴያውያን የያዙዋቸው መጻሕፍት ለብዙ ዘመናት ተጠብቀው ቆይተዋል። ከዚያ በኃላ የተነሱ የአይሁድም የክርስቲያንም ሊቃውንት እየተፈለጉ ሲገኙ ለቀኖና በመብቃታቸው ሁለተኛ የቀኖና መጻሕፍት ለመባል ችለዋል። [7]

የዲዩትሮካኖኒካል መጻሕፍት ምንጮች እና ቀኖናዊ ማረጋገጫዎች

- ❖ **መጽሐፍ ቅዱስ:-** የሀዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጸሀፊዎች ከዲዩትሮካኖኒካል መጻሕፍት እየጠቀሱ ጽፈዋል። ይኸውም መጻሕፍቱ ተአማኒነት እንዳላቸው የሚያረጋግጥ ነው። ለአብነት የሚከተሉትን ጥቅሶች መመለከት ይቻላል።

1. ይሁዳ ጌታን በሠላሳ ብር ከሸጠው በኃላ ተጸጽቶ ሠላሳውን ብር ለካህናት አለቆች መልሶላቸዋል። እነርሱም የሸክላ ሠሪን መሬት ገዝተውበታል። ይህ አስቀድሞ በነብዩ ኤርሚያስ የተነገረ ትንቢት ነው። ይህ ትንቢት አስቀድሞ ከዲዩትሮካኖኒካል መጻሕፍት አንዱ በሆነው በተረፈ ኤርያስ ተጽፏል።

"በዚያን ጊዜ በነቢዩ በኤርምያስ የተባለው። ከእስራኤል ልጆችም አንዳንዶቹ የገመቱትን የተገመተውን ዋጋ ሠላሳ ብር ያዙ፥ ጌታም እንዳዘዘኝ ስለ ሸክላ ሠሪ መሬት ሰጡት። የሚል ተፈጸመ።" ማቴ27÷9-10

"የእስራኤል ልጆች የተስማሙበት የክርስቶስን ዋጋ ሠላሳውን ብር ይቀበሉታል። ያንንም ብር ለሸክላ ሠሪ ቦታ ዋጋ አድርገው ይሰጡታል" ተረፈ ኤርሚያስ 7÷3 (1980 እትም) [8]

2. አይሁድ ጌታችንን መከራ እንዳደረሱበት፣ እንደ ዘለፉት እና ለሞት አሳልፈው እንደሰጡት በመጽሐፈ ጥበብ በትንቢት የተቀመጠውን እና በወንጌላት የተጻፈውን በማነጻጸር ማየት ይቻላል።

ትንቢት:- "የእግዚአብሔር እውነተኛ ልጅ እንደሆነ ያድነው ከሚቃወሙትም ሰዎች እጅ ያድነው" ጥበብ2÷18

---

[7]Pope Shenouda lll CD, Coptic Orthodox Church, Australia, 1988

[8]ይሁዳ ለካህናት ስለ መለሰው እና እነርሱም ለሸክላ ሰሪ ስለ ሰጡት ሠላሳ ብር በ 1980 ዓ.ም እትም ተረፈ ኤርሚያስ7፡3 ላይ ይገኛል። በ 2000 ዓ.ም እትም(አዲሱ እትም) ደግሞ ተረፈ ባሮክ1፡3 ላይ ይገኛል። በ 1980 እትም ሁለቱም ተረፈ ኤርሚያስ በሚል በአንድ ላይ ታትመው የነበረ ሲሆን በ 2000 እትም ለየብቻቸው ታትመዋል።

ፍጻሜ:- “በእግዚአብሔር ታምኖአል፤ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሎአልና ከወደደውስ አሁን ያድነው።"ማቴ 27:43

ትንቢት:- “ቅንነቱን እናውቅ ዘንድ እየሰደብን በመከራ እንመርምረው እንደ ቃሉ ረዳት ይሆነው እንደሆነ የከፋ የተዋረደ ሞትን እንፍረድበት አሉ" ጥበብ2÷19-20

ፍጻሜ:- "ኢየሱስንም የያዙት ሰዎች ይዘብቱበትና ይደበድቡት ነበር፤ ሸፍነውም ፊቱን ይመቱት ነበርና። በጥፊ የመታህ ማን ነው? ትንቢት ተናገር እያሉ ይጠይቁት ነበር።ሌላም ብዙ ነገር እየተሳደቡ በእርሱ ላይ ይናገሩ ነበር።" ሉቃ22÷63-65

3. በወንጌል ላይ ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ለመፈተን የቀረቡ ትንሳኤ ሙታን የለም የሚሉ ሰዱቃውያን እንደ ነበሩ ተጽፏል።

"ሰባት ወንድማማች በእኛ ዘንድ ነበሩ፤ ፊተኛውም ሚስት አግብቶ ሞተ፥ ዘርም ስለሌለው ሚስቱን ለወንድሙ ተወለት....ሁሉ አግብተዋታልና በትንሣኤ ቀንስ፥ ከሰባቱ ለማናቸው ሚስት ትሆናለች? ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው። ከመጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ።" ማቴ22÷24-28 ሰዱቃውያ ይህን ታሪክ ከመጽሐፈ ጦቢት ነው የወሰዱት። እነርሱ እሱን ለመፈተን ታሪኩን ቢጠቅሱትም መጻሕፍትን አታውቁምና ትስታላቹ ብሎ መልስ ሰጥቷቸዋል።

"እንሆ ሰባት ሰዎች አገቡሽ ባሎችሽ እየታነቁ እንዲሞቱ አታውቂምን? አሏት። ከነርሳቸው አንዱ እንኳን አልቀረሽም። እነርሳቸውም ሞተዋልና..." ጣቢት3÷8

4. ከጌታ ሐዋርያት ከሆኑት አንዱ ይሁዳ ሄኖክ ስለ ተናገረው ትንቢት ጽፏል። የሄኖክ ትንቢት በመጽሐፈ ሄኖክ ላይ ተጽፎ ይገኛል።

“ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነ ሄኖክ። እነሆ፥ ጌታ በሁሉ ላይ እንዲፈርድ... ሁሉ እንዲወቅስ ከአእላፋት ቅዱሳኑ ጋር መጥቶአል ብሎ ለእነዚህ ደግሞ ትንቢት ተናገረ።" ይሁ 1:14-15

"ለወዳጆቹ ይፈርድላቸው ዘንድ እንሆ ከብዙ መላእክት ጋራ ይመጣል። ሕገ እግዚአብሔርንም የዘነጉ ሰዎች ያጠፋቸዋል።" መጽሐፈ ሄኖክ 1÷9

5. ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮንቶስ መልእክቱ ከመጽሐፈ መቃብያን ጠቅሶ ጽፏል።

“ነገር ግን። ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንድተጻፈ፥ እንዲህ እንናገራለን።"1ኛቆሮ 2:9

"ለደጋግ ሰዎች የተዘጋጀች ደስ የምታሰኝ ዓይን ያለየውን ጆሮም ያልሰማውን በሰው ልብ ያልታሰበውን እግዚአብሔር ደስ ላሰኙት ያዘጋጀውን..." 1ኛመቃ14÷20

6. ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱም ከመጽሐፈ መቃብያን ጠቅሶ አስተምሯል።

“ሴቶች ሙታናቸውን በትንሣኤ ተቀበሉ፤ ሌሎችም መዳንን ሳይቀበሉ የሚበልጠውን ትንሣኤ እንዲያገኙ እስከ ሞት ድረስ ተደበደቡ፤"(ወደ ዕብራውያን 11:35)

ይህ ታሪክ በቀጥታ ከመጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ ከምእራፍ 3 የተወሰደ ታሪክ ነው። 1ኛመቃ3÷1-38 ይመልከቱ።

7. በትንቢተ ኤርሚያስ ላይ የኤርሚያስ ደቀ መዝሙር የነበረው ባሮክ ጸሀፊ እንደ ነበር ተጽፏል። ደግሞም ከኤርሚያስ የሚሰማቸውን ነገሮች ይጽፍ እንደ ነበር ተጽፏል።

"ኤርሚያስም ሌላ ክርታስ ወሰደ ለኔርያም ልጅ ለጸሐፊው ለባሮክ ሰጠው እርሱም የይሁዳ ንጉሥ የኢዮአቄም በእሳት ያቃጠለውን የመጽሐፍ ቃል ሁሉ ከኤርሚያስ አፍ ጻፈበት ደግሞም እንደ ቀድሞ ያለ ቃል ብዙ ቃል ተጨመረበት” ኤር36÷32

ይህ ሀሳብ ለመጽሐፈ ባሮክ ፍንጭ የሚሰጥ ነው። ባሮክ ጸሀፊ ከነበረ ባሮክ የጻፋቸው መጽሐፍት ወዴት አሉ? የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሳት ይቻላል።

❖ ግሪክ ሰባ ሊቃናት (Septuagint/LXX) ትርጉምና ስብስብ

- ✓ የሰባው ሊቃውንት ትርጉም በባቢሎን ምርኮ ጊዜም ሆነ ከምርኮው በኃላ በተፈጠሩ ችግሮች ወደ ግብጽ ተሰደው በዚያ በመሰረቱት የእስክንድርያ አይሁድ በበጥሊሞስ 2ኛ ፒላደልፍስ/Ptolemy II Philadelphus (285-247 ቅ.ል.ክ) ትእዛዝ ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ የተተረጎመ ነው። ይህ የሰባ ሉቃውንት ትርጉምና ስብስብ በግሪክ አናጊግሶስኮመና(anagignoskomena) ወይም ዲዩትሮካኖኒካል (deuterocanonical) መጽሐፍትን ይዘዋል።
- ✓ ይሄን በሚያጠናክር ሁኔታ በግሪክ ቋንቋ የተጻፉ ቀደምት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥራዞች(codices) መሆናቸው በሚታመነው የቫቲካን ጥራዝ (Codex Vaticans)፣ የሲናይ ጥራዝ(Codex Sinaiticus እና የአሌክሳንደርያ ጥራዝ (Codex Alexanderinus) ውስጥ የዲዩትሮካኖኒካል መጽሐፍት ከሌሎት አሥራው መጻሕፍት ጋር አብረው ይገኛሉ። [9]

---

[9]Meade, John D. (2018-03-23). "Was there a "Septuagint Canon"?”. Didaktikos: Journal of Theological Education. Retrieved8 October 2019.

Septuagint vs Masoretic Text

- ✓ አይሁድ ከክርስቶስ ልደት በፊት የታወቀ እና የተወሰነ የመጽሐፍት ብዛት የላቸውም። ለመጀመሪያ ጊዜ ከክርስቶስ በኃላ በ 90ዓ.ም በጃሚና ጉባኤ(Council of Jamina) የተሰበሰቡት ሊቃውንት ፕሮቴስታንቶች የማይቀበሏቸውን የዲዩትሮካኖኒካል መጽሐፍት ላለመቀበል ወሰኑ። በመቀጠልም ማሶሬቲክስ(Masoretic Text/MT) በመባል የሚታወቀውን የአይሁድ የብሉይ ኪዳን 39 መጽሐፍት ያሉትን ከ600ዓ.ም ጀምሮ ፈሪሳውያን አይሁዶች በገሊላ በጥብርያዶስ ባህር አጠገብ ተሰብስበው ማዘጋጀት ጀመሩ። በጃሚና የተሰበሰቡ አይሁድ የዲዩትሮካኖኒካል መጽሐፍትን ያልተቀበሉበት ሁለት ዋና መክንያቶችን ማንሳት ይቻላል። [10]

  1. የመጀመሪያው አይሁድ የራሳቸውን መጽሐፍ እየጠቀሱ መልስ ላሳጧቸው የክርስቲያን ሊቃውንት መልስ ለመስጠት ትኩረት የሰጡበት ጊዜ ነበር። የአይሁድ ጉባኤ የዲዩትሮካኖኒካል መጽሐፍት ስለ መሲሁ መምጣት፣ አለምን ለማዳን ስለ መሰቀሉ፣ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ በግልጽ ይመሰክራሉ። ይህ ደግሞ አይሁድ ለክርስቶስ ከነበራቸው አመለካከት ጋር ይጋጫል። ለራሳቸው አመለካከት ሲሉ መጽሐፍቱን ላለመቀበል ወስነዋል። ስለ መሲሁ በግልጥ የሚናገሩ የዲዩትሮካኖኒካል መጽሐፍት ለአብነት ያህል የቀረቡ:-

መጽሐፈ ጥበብ:-

"እግዚአብሔርንም ማወቅ በእኔ አለ ይላል ራሱንም የእግዚአብሔር ልጅ ያደርጋል" ጥበብ2÷13

መጽሐፈ ባሮክ

"እርሱን የሚመስል ሌላ የለምና ወደ አንተ መጣን ይላሉ።የጥበብን ሥራ ሁሉ እርሱ አገኛት ለባለሟሉ ለያእቆብ ለወዳጁም ለእስራኤል ሰጠው። ከዚህ በኃላ በምድር ተገለጠ እንደ ሰውም ሆነ።" ባሮክ3÷38

2. የአይሁድ ዳግማዊ የነጻነት እንቅስቃሴ 70ዓ.ም ከፈነዳ በኃላ የብሔራዊነት ስሜት ያየለበት ጊዜ ነበር። ይህ በመሆኑ በ 90 ዓ.ም በጃሚና ጉባኤ የመጽሐፍትን ቀኖና ለመወሰን የተሰበሰቡ አይሁድ በነበራቸው ፀረ ግሪካዊ አቋም በግሪክ ቋንቋ ብቻ ይገኙ የነበሩትን መጽሐፍት ላለመቀበል ወስነዋል።

[ለምን የሰባ ሊቃውንት ትርጉምና ስብስብ ለዲዩትሮካኖኒካል መጽሐፍት ምንጭነት ተጠቀሰ?]

---

[10]Canon of the Old Testament" .Catholic Encyclopedia.

- ✓ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከነበረበት የቤተክርስቲያን ምሥረታ ጀምሮ በቤተክርስቲያን አባቶች ዘንድ (Early Church Fathers) ተቀባይነት የነበረው የሰባ ሊቃናት ትርጉም ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት እንደ ሚናገሩት አብዛኛዎቹ በሀዲስ ኪዳን መጽሐፍት የተጠቀሱት የብሉይ ኪዳን ጥቅሶች ከሳባ ሊቃውንት ትርጉም የተወሰዱ ናቸው።በተጨማሪም በጥንቷ ቤተክርስቲያን በአብዛኛው ለትርጉም ምንጭነት እና ለማሥተማሪያነት ያገለገለው የሰባው ሊቃውንት ትርጉም ነው። የዲዩትሮካኖኒካል መጽሐፍትን አካቶ የያዘው የሰባ ሊቃውንት ትርጉምና ስብስብ በመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን ዘንድ እውቅና ያለው መሆኑ ለመጽሐፍቱ ተአማኒነት ማረጋገጫ የሚሰጥ ነው።[11]

[የአይሁድ ውሳኔ እና ፕሮቴስታንቶች]

=>>>አይሁድ መጽሐፍቱን ያልተቀበሉባቸው የራሳቸው መክንያት ያላቸው ሲሆን ፕሮቴስታንቶችም እነርሱ ካልተቀበሉ እኛም አንቀበለም ብለው አውጥተዋቸዋል። ይህ የስህተት ሀሳብ ነው።

1. ከክርስቶስ መምጣት በኃላ አይሁድነት በቀድሞው ማንነት የሚታወቅ አይደለም። አሁን በክርስትና ዘመን አይሁድ ስንል የይሁዳ ነገዶች ወይም የያእቆብ ዘሮች ወይም የአብርሃም የቃልኪዳን ልጆች ማለት አይደለም። ከክርስቶስ እርገት በኃላ ያለው አይሁድነት እውነተኛ ሳይሆን ሐሰተኞች የክርስቶስ ተቃዋሚ (Anti-Christ) እና የሰይጣን ማህበር መሆናቸውን ቅዱስ መጽሐፍ አስቀምጦታል።

“መከራህንና ድህነትህን አውቃለሁ፥ ነገር ግን ባለ ጠጋ ነህ፤ የሰይጣንም ማኅበር ናቸው እንጂ አይሁድ ሳይሆኑ። አይሁድ ነን የሚሉት የሚሳደቡትን ስድብ አውቃለሁ።"(የዮሐንስ ራእይ 2:9)

አይሁዶች እኛ ከአማኞች ወገን ነን ቢሉም የሚታመኑበት መንገድ ግን በጌታ በክርስቶስ ከሆነው የመዳን መንገድ የተለየ በመሆኑ የሰይጣን ማህበር ተብለዋል። ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ እንዲህ ይላል:-

"በግልጥ አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ አይደለምና፥ በግልጥ በሥጋ የሚደረግ መገረዝም መገረዝ አይደለምና ዳሩ ግን በስውር አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ ነው፥ መገረዝም በመንፈስ የሚደረግ የልብ መገረዝ ነው እንጂ በመጽሐፍ አይደለም።" ሮሜ2÷28-29

=>>>የጥንቷ ቤተክርስቲያን ሊቃውንት ከሐዋርያት በተማሩት መሰረት ይህንን የቅዱስ ጳውሎስ ጥቅስ አብራርተውታል። የሁሉም አረዳድ ከክርስቶስ መወለድ በኃላ ያሉት የአይሁድ ማህበር ሀሰተኛ እንደሆነና እና በፊደል ሳይሆን በመንፈስ የሚመላለሱ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ሕግ የሚፈጽሙ በስሙም የተሾሙ እስራኤል ዘነፍስ እነርሱም የክርስቲያኖች ማህበር የሆነችው ቤተክርስቲያን ባለ ሙሉ ስልጣን እንደሆነች ነው።

[11] Nicole, Roger, New Testament Use of the Old Testament Revelation and the Bible, ed. Carl. F.H. Henry (Grand Rapids: Baker, 1958), pp. 137–51.

ለዚህም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ (St. John Chrysostom)፣ ሊቁ አርጌንስ (Origen the Scholar)፣ ቅዱስ ጎርጎሪዮስ(St. Gregory the Theologian) ተጠቃሽ ናቸው። [12] በተጨማሪም ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበሩት አይሁዶች ወጥ የሆነ የመጽሐፍት ብዛት አልነበራቸውም። ፈሪሳውያን አይሁድ፣ ሰዱቃውያን አይሁድ፣ ኤስንያን አይሁድ፣ ሳምራውያን እና ቤተ እሥራኤል በሚጠቀሙት ቅዱሳት መጽሐፍት ይለያያሉ። በሀዲስ ኪዳን ባለ ሙሉ ስልጣን የሆነችው ቤተክርስቲያን እንጂ የሀሰተኞች ማህበር የሆነው የአይሁድ ስብስብ አይደለም። ይህ በሆነበት ሁኔታ ከመሲሁ መገለጥ በኃላ የተወሰነን የአይሁድ ውሳኔ ትክክል ነው ብሎ የቤተክርስቲያን መጽሐፍትን አለመቀበል የአይሁድ ፀረ ክርስቶሳዊ ሀሳብ መደገፍ ነው። ለዚህ ነው መጽሐፍ እንዲህ ሲል ያስጠነቀቀን:-

“ኢየሱስም። ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠንቀቁና ተጠበቁ አላቸው።" የማቴዎስ ወንጌል 16:6

2. ፕሮቴስታንቶች የአይሁድ ውሳኔ ትክክል ነው ብለው መቀበላቸው ራሳቸውን ችግር ውስጥ ይከታቸዋል። መክንያቱም አይሁድ የዲዩትሮካኖኒካል መጽሐፍትን አንቀበልም ብለው ያበቁ ሳይሆን በ 66ቱ ውስጥ ከሚገኙት 39ኙ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትም ብዙ ነገር ሰርዘዋል። ለአብነት የሚከተሉትን መመልከት ይቻላል:-

- " እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፥ ትርጓሜውም። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው።" የማቴዎስ ወንጌል 1:23

ይህ ትንቢት ከትንቢተ ኢሳይያስ 7÷14 የተወሰደ ነው። በአይሁድ Masoretic መጽሐፍ ድንግል የሚለውን ወጣት ሴት young woman ይለዋል።

- " ስለዚህ ወደ ዓለም ሲገባ። መሥዋዕትንና መባን አልወደድህም ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ፤"

(ወደ ዕብራውያን 10:5) ይህ የትንቢት ቃል የተወሰደው ከመዝሙር 40÷6 ነው። በአይሁድ Masoretic ስጋን አዘጋጀህልኝ የሚለው የለም።

=>>>ከዚህ የምንረዳው አይሁድ የዲዩትሮካኖኒካል መጽሐፍትን አለመቀበል ብቻ ሳይሆን ከፕሮቶካኖኒካል መጽሐፍትም ብዙ ለውጥ ማድረጋቸውን ነው።

_____

[12] The Epistle of St Paul to the Romans. Based on the interpretation & Meditations of the Early Fathers by: - Fr Tadros, Yacoub Malaty. Page 52-54

[መጽሐፈ ሄኖክና መጽሐፈ ኩፋሌ]

አንዳንድ ሰዎች መጽሐፈ ሄኖክና መጽሐፈ ኩፋሌ በኢትዮጵያ ብቻ ስለሚታወቁ ተቀባይነት የላቸውም ይላሉ። ይህ ግን የስህተት ሀሳብ ነው።

- ✓ መጽሐፈ ሄኖክ(Book of Enoch):- በሀዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ በሐዋርያው ይሁዳ ተጠቅሷል። ይሁዳ1÷14 እና ሄኖክ 1÷9 ተመልከቱ። በኢትዮጵያ ብቻ ይታወቃል የሚለውን ሀሳብ የሚያፈርስ አዲስ ግኝት ተገኝቷል። ይኸውም የሙት ባህር ጥቅል (Dead See Scrolls) በመባል የሚታወቁት በቁምራን ዋሻ ውስጥ የተገኙት የቅዱሳት መጻሕፍት ስብስብ ነው። መጽሐፈ በአርማይክ (Aramaic)፣ በኩይኔ ግሪክ(Koine Greek) እና በላቲን (Latin) ቋንቋዎች የተጻፉ የመጽሐፈ ሄኖክ ቁርጥራጮች ተገኝተዋል። በዚህም መጽሐፉ አስቀድሞ በአይሁድ ዘንድ የታወቀ እንደሆነ ማረጋገጫ የሰጠ ነው። በተጨማሪም በተለያዩ የ 1ኛና የ2ተኛ ክ/ዘመን ደራሲዎች እንደተጠቀሰ ይታወቃል። [13]
- ✓ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት መጽሐፉን ስላላገኙት በቀኖና ውስጥ ባይከቱትም ኢትዮጵያ መጽሐፉ በእጇ ስላለ እና በራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት ያለው ብሎም ከሌሎች ቅዱሳት መጽሐፍት ጋር የሚስማማ ስለሆነ በቀኖና ውስጥ ከታዋለች።
- ✓ መጽሐፈ ኩፋሌ (Book of Jubilees) :- የዚህ መጽሐፍ ጸሀፊ ሙሴ እንደሆነ ይታመናል። ይህንንም በመጽሐፉ ይዘት ማረጋገጥ ይቻላል። ይህም መጽሐፍ ልክ እንደ መጽሐፈ ሄኖክ በሙት ባህር ጥቅሎች (Dead see scrolls) ተገኝቷል። ይህም ልክ እንደ መጽሐፈ ሄኖክ አስቀድሞ ይታወቅ እንደ ነበር የሚያሳይ ነው። በተጨማሪም በቀደምት የቤተክርስቲያን አባቶች ለማስተማሪያነት እንደ ተጠቀሰ ይነገራል። ለአብነትም ኤጲፋኔዎስ (Epiphanius) ፣ ጀስቲን (Justin Martyr), አርጌንስ(Origen) , የታርሱሱ ዲዮዶሮስ(Diodorus of Tarsus) ይጠቀሳሉ። [14]
- ✓ በተጨማሪም በሙሴ ኦሪት መጻሕፍት የማይገኙ ግን በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱ ጥቅሶች አሉ። ለምሣሌ:- " ሙሴም። እጅግ እፈራለሁ እንቀጠቀጥማለሁ እስኪል ድረስ የሚታየው እጅግ የሚያስፈራ ነበር፤" (ወደ ዕብራውያን 12:21) መመልከት ይቻላል። ይህ በሆነበት ሁኔታ ከአምስቱ የሙሴ መጽሐፍት ውጪ የሆነ ተቀባይነት የለውም ብሎ መደምደም አይቻልም። ቅድስት ቤተክርስቲያን በትውፊት በደረሳት መሠረት መጽሐፉን በቀኖና ውስጥ ከታ ትጠቀምበታለች።

---

[13] Cheyne and Black, Encyclopaedia Biblica (1899), "Apocalyptic Literature" (column 220)

[14][Charles, R. H. (1902). The book of Jubilees or the Little Genesis. London: Adam and Charles Black. pp. lxxvii–lxxxvi.]

=>>>በተጨማሪም በ Dead See Scrolls መጽሐፈ ሲራክ፣ ተረፈ ኤርሚያስ ያሉ የዲዩትሮካኖኒካል መጽሐፍት ተገኝተዋል።

❖ የሐዋርያት ቀኖና (Apostolic Canon/Ecclesiastical Canons)

ይህ አብዛኛው ቀኖናው በሐዋርያት እንደ ተጻፈ የሚታመነው የሐዋርያት ቀኖና የቤተክርስቲያን አስተዳደርን እና ሥርአትን በሚመለከት 85 ቀኖናዎችን የያዘ ነው። ሐዋርያት እንደ ጳጉት እስከ አሁን በትክክል ማረጋገጥ ባይቻልም ከምሥራቅ ቤተ-ክርስቲያን ልምድ ስንነሳ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት የሐዋርያትን ትምህርትና ሥርአት ይዘው በመገኘታቸው ለሥርአተ አምልኮ ጥቅም ላይ ውለዋል። ይህን ሐዋርያውያት ቀኖና በ691 በትሩሎ በተጠራው በምስራቅ ሲኖዶስ (Eastern Council in Trullo) ተቀባይነት አግኝቷል። [15] ሐዋርያውያት ቀኖናት በአሁኑ ቅርጻቸው ተቀነባብረው ሊገኙ የቻሉበት (ለአገልግሎት በሚመች መልኩ) የጊዜ መነሻቸው (Terminus a quo) ሁለተኛ ክ/ዘመን አጋማሽ ሲሆን የተጠናቀቁት ደግሞ (Terminus ad quem) በ 3ኛው ክ/ዘመን መጨረሻ ነው።

በዚህ ሐዋርያውያት ቀኖናት የቀኖና መጻሕፍት ዝርዝር (List of Canonical Books) ይገኛል። በዚህ በ 85ኛ ቀኖና የዲዩትሮካኖኒካል መጽሐፍት አካል የሆኑት የመቃብያን መጽሐፍት እና መጽሐፍተ ዕዝራ ይገኛሉ። መጽሐፈ ሲራክም በቤተክርስቲያን ሊነበቡ ከሚችሉ መጽሐፍት ዝርዝር ውስጥ ተካቷል። [16]

የተለያዩ የተደረጉ ሲኖዶሳውያት ጉባኤዎች

1. የሂፖ ጉባኤ (Synod of Hippo):- ይህ በሰሜን አፍሪካ በ 393 ዓ.ም የተጠራው ጉባኤ የቅዱሳት መጽሐፍትን ቀኖና ዝርዝር አስቀምጧል። ይህ ጉባኤ የዲዩትሮካኖኒካል መጽሐፍትን በመቀበል በቀኖና ውስጥ ከቷቸዋል። [17]

2.የካርቴጅ ጉባኤ (Council Carthage):- በ 397 ዓ.ም የተካሄደው የካርቴጅ ጉባኤም የቅዱሳት መጻሕፍትን ቀኖናን አስቀምጧል። የዚህ ቀኖና የመጀመሪያ የመረጃ ምንጭ ስለ ጉባኤው የሚያትተው "Codex Canonum Ecclesiae Africanae” ነው። በዚህ ቀኖና ውስጥ መጽሐፈ ዮዲት፣ መጽሐፈ ጦቢት፣ መጽሐፍተ መቃብያን፣መጽሐፍተ እዝራ፣ መጽሐፈ ጥበብ ያሉ የዲዩትሮካኖኒካል መጻሕፍት ተካተዋል። [18]

---

[15] Canons, Apostolic , 1910 New Catholic Dictionary , accessed 16 April 2016.

[16] El-satic El-Assal the Collection of canons Chapter 2

[17][Augustine of Hippo. On Christian Doctrine. Book II, Chapter 8.

[18] http://www.bible-researcher.com/canon8.html

- ❖ በቤተክርስቲያን ታሪክ ቀደምት የሆኑት የቅድመ ኒቂያ (Anti Nicen Fathers) እና ድኅረ ኒቂያ (Post Nicen Fathers) የዲዩትሮካኖኒካል መጽሐፍትን ተቀብለው ለሃይማኖት ማስተማሪያ ለመሠረተ እምነት(ዶግማ) ማስረጃ፣ ለመናፍቃን መልስ መስጫ ተጠቅመውባቸዋል። ይህንንም በጻፏቸው መጻሕፍትና በላኪቸው መልእክቶች ማረጋገጥ ይቻላል። ለአብነት ያህል ጥቂቶችን እንመልከት፡-

- ቀለሜንጦስ ዘሮም (Clement of Rome), [To the Corinthians 27:5 (A.D 80)] ላይ ከመጽሐፈ ጥበብ 12÷12 ጠቅሶ ጽፏል።
- ቅዱስ ፖሊካርፐስ (St. Polycarp), [to the Philippians, 10 (A.D 135)] ላይ ከመጽሐፈ ጦቢት 4÷10 ጠቅሶ ጽፏል።
- ቅዱስ ሄሬኔዎስ (St. Irenaeus), [Against Heresies V:35:1(A.D 180)] ላይ ከመጽሐፈ ባሮክ 4÷36 ጠቅሶ ጽፏል።
- ሊቁ ጠርጡለስ (Tertullian), [Prescription against the Heretics, 7 (A.D 200)] ላይ ከመጽሐፈ ጥበብ ጠቅሶ ጽፏል።
- ቅዱስ ሂፖሊተስ (St. Hippolytus), [Commentary on Daniel, 6÷1 (A.D 204)] ላይ ከመጽሐፈ ሶስና ጠቅሶ ጽፏል።
- ሊቁ አርጌንስ (Origen), [Fundamental Principles, 2:2 (A.D 230)] ላይ ከ2ኛ መቃ ጠቅሶ ጽፏል።
- ቅዱስ ቄርሎስ ዘእየሩሳሌም (St. Cyril of Jerusalem), [Catechetial Lectures, 9÷23(A.D 350)] ላይ መዝሙር ዘሰለስቱ ደቂቅ ጠቅሶ ጽፏል።
- ቅዱስ ጎርጎሪዮስ ዘእንዚናዙ (St. Gregory of Nazianzen), [Orations 45, 2nd Oration of Easter 15 (A.D 383)] ላይ ከመጽሐፈ ዮዲት5÷6 ጠቅሶ ጽፏል።
- ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ (St John Chrysostom), [Homilies on John, 48 (A.D 391)] ላይ ከመጽሐፈ ሲራክ10÷9 ጠቅሶ ጽፏል።
- ቅዱስ ጀሮም(St. Jerome), [to Paulinus, Epistle 58 (A.D 395)] ላይ ከመጽሐፈ ጥበብ4÷9 ጠቅሶ ጽፏል።
- የአቁሊያው ሩፊኖስ (Rufinus of Aquileia), [The Apostolic Creed, 37-38(A.D 404)] ላይ ከባሮክ3÷36-38 ጥቅሶችጽፏል።

[ቅዱስ አትናቴዎስ ስላልተቀበላቸው እኛም አንቀበልም የሚለው የፕሮቴስታንቶች ሙግት ሲመዘን]

- ✓ ፕሮቴስታንቶች ቅዱስ አትናቴዎስን በመጥቀስ የ Deutrocanonical መጽሐፍትን ስላልተቀበለ እኛም አንቀበልም የሚል ሀሳብ ያቀርባሉ። ኦርቶዶክሳዊውን አባት ለኦርቶዶክሳዊውን ለመንቀፍ ይጠቀሙበታል። ቅዱስ አትናቴዎስ በ 367ዓ.ም በላከው 39ኛ የፋሲካ በአል መልእክቱ አምላካውያት መንፈሰ እግዚአብሔር ያለባቸውን መጽሐፍ ዘርዝሯል። መጽሐፍቱንም ከዘረዘረ በኃላ " እነዚህ የተጠማ በውስጣቸው በሚገኙ ቃላት ይረካ ዘንድ የእውነተኛ የደኅንነት ምንጮች ናቸው። በእነዚህ ብቻ የቅድስና ትምህርት ይሰበካል።" በማለት ተናግሯል። [ዲበኩሉ ዘውዴ 81 ቅዱሳት መጻሕፍት ምንጮች-ቀኖናት ገጽ-51] ፕሮቴስታንቶች ይህንን ይዘው መጽሐፍቱን አንቀበልም የሚል ሙግት ያቀርባሉ። በዚህም ራሳቸውን ወጥመድ ውስጥ ይከታሉ።

1. ቅዱስ አትናቴዎስ በዘረዘራቸው ዝርዝር ውስጥ ፕሮቴስታንቶች የማይቀበሏቸውን መጽሐፈ ባሮክ እና ተረፈ ኤርሚያስ ይገኛሉ። እነርሱ ቅዱስ አትናቴዎስ የተቀበላቸውን እንቀበላለን ካሉ ለምን እነዚህን አልተቀበሏቸውም?

2. ቅዱስ አትናቴዎስ መጽሐፈ አስቴርን ከብሉይ ኪዳን የቀኖና መጽሐፍት ዝርዝር ውስጥ አላስገባውም። ፕሮቴስታንቶች መጽሐፈ አስቴርን ተቀብለው ከብሉይ ኪዳን ቀኖና ውስጥ ከተው ይጠቀሙበታል። ይህ ከሆነ ቅዱስ አትናቴዎስ ያልተቀበለውን ለምን ተቀብለው አስገቡ?

- ✓ ቅዱስ አትናቴዎስ በቀኖና የሚካተቱትን መጽሐፍት ከዘረዘረ በኃላ እንዲህ ይላል "በእርግጥ ስለ በለጠ እርግጠኝነታቸው ከእነዚህ በስተቀር ከሚቀነኑት መጽሐፍት ጋር ያልሆኑ ነገር ግን ኢዲስ ለሚመጡትና ትምህርተ ቅድስናን ለሚፈለጉ ይነበቡ ዘንድ በአባቶች የታዘዙ ሌሎች መጽሐፍት እንዳሉ አስፈላጊ መሆኑን እጨምራለው። እነዚህም መጽሐፈ ሲራክ፣ መጽሐፈ ጥበብ፣ መጽሐፈ አስቴር፣ መጽሐፈ ዮዲት፣ መጽሐ ፈ ጦቢትና ትምህርተ ሐዋርያት ናቸው።" [19]

1. ቅዱስ አትናቴዎስ አስቀድሞ ስለ ቅድስና በእነዚህ ብቻ ይሰበካል ካለ በኃላ የዲዩትሮካኖኒካል መጽሐፍት ስለ ቅድስና ለመማር መነበብ እንደሚችሉ መናገሩ መጽሐፍቱ እውነተኞች እና የሚታመኑ እንደሆኑ ያሳያል።

---

[19] Auwers, Jean-Marie; de Jonge, H. J., eds. (2003). The Biblical Canons . Peeters Publishers. p. 267. ISBN 978-90-4291154-3

2. ቅዱስ አትናቴዎስ ያቀረበው መነሻ ሀሳብ ሲሆን በወቅቱ ሙሉ ለሙሉ ቀኖናቸውን አልፈዋል ብሎ ያመነባቸውን መጽሐፍት (κανονικα) በቀኖና መልክ አስቀምጧቸዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና በቅዱስ አትናቴዎስ ዝርዝር ብቻ ያልተመሠረተ ነው። ለዚህም ነው ከቅዱስ አትናቴዎስ ጋር ህብረት ያላቸው ከእሱ በፊት የነበሩ፣ በእሱ ዘመን የነበሩ፣ ከእሱ በኃላም የተነሱ ሌሎች የቤተክርስቲያን አባቶች መጽሐፍቱን ተቀብለው ለሃይማኖት ማሥተማሪያ የተጠቀሙባቸው። ከላይ የዘረዘርናቸው የቤተክርስቲያን አባቶች ተጠቃሽ ናቸው።

3. ፕሮቴስታንቶች መጽሐፍቱን የተለያየ መክንያት እያነሱ ይተቻሉ፣ ግን መጽሐፍቱን ቅዱስ አትናቴዎስ ስለ ቅድስና የሚሰብኩ በቤተክርስቲያን ሊነበቡ የሚገባቸው ብሎ ማስቀመጡን አላስተዋሉም።

የሐዲስ ኪዳን የሥርአት መጻሕፍት (Books of Church Orders) ምንጮች

የሥርአት መጻሕፍት የሚባሉት 27ቱን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ወደ 35 የሚያደርሱት 8ቱ መጻሕፍተ ሐዲሳት ናቸው። አጠቃላይ መጠሪያቸው ስምንቱ ብሔረ ቀኖናት ዘቀለሜንጦስ ወይም ሲኖዶስ ዘቅዱሳን አበዊነ ሐዋርያት የሚል ነው። ሥርአቶቹን የሰሯቸውና የደነገጓቸው ቅዱሳን ሐዋርያት ሲሆኑ በእነርሱ ትምህርትና ትእዛዛት ላይ ተመሥርተው በጽሁፍ የቀረጿቸውና ያቀነባበሯቸው ደግሞ ከአንደበታቸው የተማሩ በእጃቸው የተሾሙ በእግራቸው የተተኩ ሐዋርያዊያን አበው (Apostolic Fathers) ናቸው። የቅንብራቸው መነሻ ጊዜ (Terminus a Quo) የ 2ተኛው ምዕተ አመት አጋማሽ ሲሆን መፈጸሚያው ደግሞ (Terminus end Qucm) ሶስተኛው ምእተ አመት መጨረሻ ነው። ለስምንቱ መጻሕፍት ቅንብር መሠረት የኾኑት የሚከተሉት ናቸው።

1.የሐዋርያት ቀኖና (Apostolic Canon/Ecclesiastical Canons):- ይህ አብዛኛው ቀኖናው በሐዋርያት እንደ ተጻፈ የሚታመነው የሐዋርያት ቀኖና የቤተክርስቲያን አስተዳደርን እና ሥርአትን በሚመለከት 85 ቀኖናዎችን የያዘ ነው። ሐዋርያት እንደ ጻፉት እስከ አሁን በትክክል ማረጋገጥ ባይቻልም ከምሥራቅ ቤተ-ክርስቲያን ልምድ ስንነሳ 85 ሐዋርያውያት ቀኖናት የሐዋርያትን ትምህርትና ሥርአት ይዘው በመገኘታቸው ለሥርአተ አምልኮ ጥቅም ላይ ውለዋል። ይህን ሐዋርያውያት ቀኖና በ691 በትሩሎ በተጠራው በምስራቅ ሲኖዶስ (Eastern Council in Trullo) ተቀባይነት አግኝቷል።

2. ዲደኬ ትምህርተ ሐዋርያት (The Didache):- ሙሉ የመጽሐፉ ስም "በዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ለአሕዛብ የተሰጠ የጌታ ትምህርት/ Teaching of the Lord by the Twelve Apostles to the Gentiles" የሚል ነው።

ኦደስት (Adust) የተባለ አጥኚ ዲዳኬ ከ50-70 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት እንደ ተጻፈ በጥናቱ አሳይቷል። [20] ከ 8ቱ የሥርአት መጻሕፍት አንዱ የሆነው እና ከ Apostolic Constitution ተወስዶ የተቀናበረው መጽሐፈ ዲድስቅልያ ከዲዳኬ ውስጥ የወሰዳቸው ንባቦችና ትምህርቶች አሉት።

3. ከትንሳኤው እስከ እርግቱ ድረስ ለ 40 ቀናት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማራቸው ትምህርቶች:- የሐዋርያት ሥራ ጸሀፊ ቅዱስ ሉቃስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ ከተነሳ በኃላ ደቀ መዛሙርትን እንደ አስተማራቸው ጽፏል።

“ደግሞ አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔርም መንግሥት ነገር እየነገራቸው፥ በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው።" የሐዋርያት ሥራ 1:3 የዚህ ትምህርት ስብስብ መጽሐፈ ኪዳን (Books of Covenant) በሚል በ 8ቱ የሥርአት መጽሐፍት ውስጥ ይገኛል።

4. መጽሐፈ ቀሌምንጦስ:- ቅዱስ ቀሌምንጦስ ዘሮም (St. Clement of Rome) ከሐዋርያት በኃላ ከተነሡትና በትምህርታቸውም ለቤተክርስቲያን ማኅቶት ከሆኑት አባቶች ውስጥ ቀዳሚው ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በፊልጵስዩስ መልእክቱ "ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት ከቀሌምንጦስና ደግሞ..." ሲል ስሙን የጠራው ይህንኑ የሮም ሊቀ ጳጳስ እንደ ሆነ ሊቁ አውሳብዮስ(Eusebius) ፣ ቅዱስ ይሩማሲስና (St. Jerome) ሊቁ ኦሪገን(Origen) ይገልጻሉ። [21] መጽሐፈ ቀለሜንጦስ ከስምንቱ የሐዲስ ኪዳን የሥርአት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኝ ነው።

ቅዱሳን ሐዋርያት በተሰበሰቡ ጊዜ ሁሉ ስለ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን፣ ስለ ካህናት አገልገሎት፣ ስለ ምእመናን ድርሻ፣ ስለ ቤተክርስቲያን አስተዳደር ውሳኔዎችን አስቀምጠዋል። ይኸውም የቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዝሙር በነበረው በቀለሜንጦስ እጅ ለካህናት እና ለምእመናን ትልከዋል።

=>>>በመጽሐፍ ቅዱስ ሐዋርያት በዘመናቸው የተለያዩ ሥርአትን እንደሰሩ ይናገራል። በ50ዓ.ም በእየሩሳሌም ተሰብስበው የሰሩት ሥርዓት በሐዋርያት ሥራ ተመዝግቦ ይገኛል። ሐዋ15÷1-29 ይህንን የሰሩትን ስርአት ምእመናን ይጠብቁቸው ዘንድ ሰተዋቸዋል።

“በከተማዎችም ሲዞሩ በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያትና ሽማግሌዎች የቈረጡትን ሥርዓት ይጠብቁ ዘንድ ሰጡአቸው።" የሐዋርያት ሥራ 16:4

---

[20] J-P Audst, LA Didache: Instruction des Apotres. (Paris: Etudes Bibliques, 1958)

[21] Eusebius, Hist. Eccl. 2.6.3 (Lake, LCL); Jerome, Dir. 1ll. 15(NPNF 2/3: 366); Origen , Fr. Jo. 1.29 (ANF 9:378)

=>>>ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ በላከው መልእክቱ ቅዱስ ስጋውን እና ክቡር ደሙን ለመቀበል ስለ ሚገባ ጥንቃቄ ጽፎላቸው ነበር። የቀረውን ሥርአት ወደ ቆሮንቶስ ሲሄድ እንደ ሚሠራላቸው ነግሯቸዋል። የሰራላቸው ሥርአት በመጽሐፍ ቅዱስ አልተጻፈም። ነገር ግን በቤተክርስቲያን የስርአት መጻሕፍት ተጽፎ ይገኛል።

“ማንም የራበው ቢኖር ለፍርድ እንዳትሰበሰቡ በቤቱ ይብላ። የቀረውንም ነገር በመጣሁ ጊዜ እደነግጋለሁ።"1ኛቆሮ 11:34

=>>>በተጨማሪም ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቲዎስ በጻፈለት መልእክት ዲያቆናትና ኤጲስ ቆጶሳት አገልግሎት ለመታጨት ምን መሆን እንዳለባቸው እና ስለ አገልግሎት ድርሻቸው ጽፎለታል። 1ኛጢሞ3÷1-13

=>>>ከላይ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጹት ሥርአቶች በአራቱ መጻሕፍተ ሲኖዶስ ሰፍረው ይገኛሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ በትንሹ ተጽፈው የሚገኙት ሥርአቶች በእነዚህ መጻሕፍት ተብራርተው እና ተሟልተው ይገኛል። እነዚህ መጻሕፍት ሥርአተ ጽዮን ሲኖዶስ፣ አብጥሊስ ሲኖዶስ፣ ትእዛዝ ሲኖዶስ እና ግጽው ሲኖዶስ ይባላሉ።

=>>>የተቀሩት አራቱ ካላይ የተገለጹት 1ኛ መጽሐፈ ኪዳን፣ 2ኛ መጽሐፈ ኪዳን፣ መጽሐፈ ዲድስቅልያ እና መጽሐፈ ቀሌምንጦስ ናቸው። እነዚህ 8ቱ የስርአት መጻሕፍት ቱውፊታውያን በሆኑ አብያተ ክርስቲያናት (Eastern Orthodox, Oriental Orthodox እና Catholic) ዘንድ በሥርአተ አምልኮ (Liturgy) ውስጥ አገልገሎት ላይ የሚውሉ ናቸው። [22]የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በቀኖና ተክርስቲያን ውስጥ አስገብታ ትገለገልባቸዋለች። በዚህም በአለም ደረጃ Broader Canon ያላት ቤተክርስቲያን እንደሆነች ይነገርለታል።

በሌላ መርሃ ግብር (በክፍል ሁለት) የተሃድሶ መናፍቃን የ 80 አሃዱ መጻሕፍት በሆኑት የዲዩትሮካኖኒካል መጻሕፍት ላይ ለሚያነሷቸው ጥያቄዎች ምላሽ ይዘን እንመጣለን።

ስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር!

---

[22] Samuel A.B. Merce. The Ethiopic Liturgy: Its Source l, Development and Present Form